# <u>እውነተኛ ታሪክ</u>

ይህ ከረጅም ዘመናት በፊት የሆነ እውነተኛ ታሪክ ነው፡፡ ይህ ለብዙ ሰዎች እጅግ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ታሪኮች አንዱ ነው፡፡ ከረጅም ዘመናት በፊት ከተነገሩ እጅግ አስፈላጊ ታሪኮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ እኔ ይህንን ታሪክ በምናገርበት ጊዜ ይህ ታሪክ ለምን እጅግ በጣም አስፈላጊ ሆነ ብላችሁ ራሳችሁን ጠይቁ፡፡

ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ኒቆዲሞስ የተባለ አንድ ሰው ነበር፡፡ እሱ ፈሪሳዊ ሲሆን የአይሁድ ሸንጎ አለቃ ነበር፡፡ በምሽት ወደ ኢየሱስ መጥቶ፡- ‹‹መምህር ሆይ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህ ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለም መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን›› አለው፡፡

ኢየሱስም መልሶ፡- ‹‹እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም›› አለው፡፡

ኒቆዲሞስም፡- ‹‹ ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማህፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን?›› አለው፡፡

ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- ‹‹እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችለም፡፡ ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው፡፡ ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልኩህ አትደነቅ፡፡ ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፤ ድምፁንም ትሰማለህ፤ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንደሚሄድ አታውቅም፡፡ ከመንፈስ የተወለደ እንደዚህ ነው፡፡››

ኒቆዲሞስ መልሶ፡- ‹‹ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?›› አለው፡፡

ኢየሱስ መልሶ፡- ‹‹አንተ የእሥራኤል መምህር ስትሆን ይህን አታውቅምን? እውነት እውነት እልሃለሁ የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን፤ ምስክራችንንም አትቀበሉትም ስለምድራዊ ነገር በነገርኳችሁ ጊዜ ካላመናችሁ ስለ ሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ?››

በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና፤ ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና፡፡

ይህ የእግዚአብሔር ቃል ታሪክ ነው፡፡

## <u>የመጀመሪያዎቹ ውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ይህ ታሪክ ለምን በጣም አስፈላጊ ሆነ?
2. የዚህ ታሪክ ዋና ሀሳብ ምንድነው?

**<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>**

1. ኒቆዲሞስ ስለ ኢየሱስ የበለጠውን እንዲያውቅ ያነሳሳው ምንድነው?
2. ኒቆዲሞስ በምሽት ወደ ኢየሱስ የመጣው ለምነድነው?
3. ኒቆዲሞስ መንፈሳዊ እውነት ለመረዳት የተቸገረው ለምንድነው?
4. አንድ ሰው መንፈሳዊ እውነት ለመረዳት ምን ያህል ዋጋ ይከፍላል?
5. ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለ መግባት ከዚህ ታሪክ ምን እንማራለን?
6. ኢየሱስ የነፋስን ምሳሌ ሲጠቀም ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን ለማስተማር ፈልጎ ነው?
7. አንድ ሰው የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ማድረግ ያለበት ምንድነው?
8. ከዚህ ታሪክ በመነሳት እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን ወደ ዓለም የላከው ለምንድነው?
9. ዳግመኛ መወለድ ማለት ምን ማለት ነው?
10. የዚህ ታሪክ እውነተኛ መልዕክት በሕይወትህ ተፈጽሟል?